ሁለት ኃያላን መንግሥታት፣ ማለትም የኢራን ንጉሥና የኦቶማን ንጉሠ ነገሥት፣ ባሃኦላህንና ትምህርቶቹን ለመቃወም ከፍተኛ ጥረት አደረጉ። ነገር ግን የእውነት ብርሃን በቀላሉ የሚጠፋ አይደለም። ይህን እሳት ለማጥፋት በላዩ ላይ የሚደፋው ውሃ ወደ ነዳጅነት ተለውጦ የበለጠ እሳቱን አፋፋመው። እየገነነ የሄደውን የባሃኦላህን ታዋቂነት ለማቆም ምንም ማድረግ አልተቻለም። ባለስልጣኖቹ የበለጠ ሩቅ ቦታ ባጋዙት ቁጥር ወደ ትምህርቶቹ የሚሳቡና፣ ብርታቱንና ግርማውን የሚያውቁ ሰዎች ቁጥር እየበዛ ሄደ። የማያቋርጥ ጭቆና ቢደርስበትም ከአርባ ዓመታት ለበለጠ ጊዜ ባሃኦላህ የእግዚአብሔርን ቃል መግለጹን ቀጠለ። ወደ እዚህ ዓለምም እጅግ በጣም ከፍተኛ ፍቅርና መንፈሳዊ ኃይል ከማምጣቱ የተነሳ የእምነቱ ድል የተረጋገጠ ሆኗል።

የባሃኢ እምነት በአሁኑ ወቅት (2008) በ191 ነጻ አገሮችና በ45 ሌሎች አገር መንግሥት በሚተዳደሩ አገሮች ተስፋፍቷል። በመላው ዓለም ባሃኢዎች የሚኖሩባቸው 101,969 አካባቢዎች አሉ። የባሃኢ ጽሑፎች ከ800 ቋንቋዎች በላይ ተተርጉመዋል።

## የባሃኢ ሕግጋትና ትዕዛዛት

እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ግልጸት የሰው ልጅ በትክክለኛው መንገድ እንዲመራ ሕግጋትና ትዕዛዛትን ያመጣል። ከእነኚህ ሕግጋትና ትዕዛዛት አንዳንዶቹ ዘለዓለማዊ ናቸው። ሌሎች ደግሞ የሰው ልጅ ባደገና በተሻሻለ ቁጥር ይለወጣሉ።

ባሃኦላህ እንደሚነግረን የእርሱ ሕግጋት፡-
“በአገልጋዩቼ መካከል የፍቅራዊ እንክብካቤ ብርሃኖችና ለፍጡራኔ የምህረቴ ቁልፎች ናቸው። ትዕዛዛቴን ለውበቴ ፍቅር ስትሉ ጠብቋቸው” ብሎናል።

### ፀሎት፡-

በምድር ላይ ሲኖር የሰው ልጅ በየቀኑ ምግብ መመገብ አለበት። ይህ ለሰው አካል አስፈላጊ ነው። ስለዚህ መመገብ በምድራዊ ኑሮአችን መታዘዝ ያለብን ሕግ ነው። በተመሳሳይ መንገድ ከባሃኦላህ ትዕዛዛት መካከል አንዱ በየቀኑ መጸለይ እንዳለብን ነው።

እንደአካላችን ሁሉ ነፍሳችንም ሁልጊዜ ምግብ ያስፈልገዋል። የነፍስ ምግብ ደግሞ ፀሎት ነው፤ ጸሎት ከአምላክ ጋር ማውጋት ነው።

### ፃም

ጾም ከሥጋዊ ፍላጎት የመጠበቅ ምልክት ነው። ጾም ምሳሌና አስታዋሽ ነው። ይህም ማለት ሰው ከምግብ ፍላጎት እንደሚከለከል ሁሉ ከግላዊ ምኞትና ፍላጎትም መጠበቅ ይገባዋል ማለት ነው።

### ሐሜት

ባሃኦላህ ሐሜትና ስም ማጥፋትን ይከለክላል። አንድነት እንዳይኖረን ካሉት እጅግ በጣም ታላላቅ ጠላቶች አንዱ ሐሜት ነው።

ባሃኦላህ ሲናገር፡-

የዙፋኔ ጓደኛ ሆይ!
*ክፉ ነገር አትስማ መጥፎ ነገርንም አትይ፤ ራስህን አታዋርድ፣ እንዲሁም አትዘን፣ አታልቅስ። ክፉ ነገር አትናገር፣ በአንተም ላይ ሲነገር እንዳትሰማ፤ የሌሎችን ስህተት አታጉላ፣ የራስህ አይሎ እንዳይታይብህ፤ የማንንም ውርደት አትመኝ፣ የራስህ ወራዳነት እንዳይገለጽብህ። እንግዲህ በነጻነትና በእርካታ፣ ይህንን ሟች አካል ጥለህ ወደ ረቂቋ ገነት ተመልሰህ በማይጠፋው መንግሥት ለዘለዓለም ትኖር ዘንድ፣ ከመቅጽበት ከሚያልፍ ጊዜ ያነሱትን የሕይወትህን ቀኖች፣ በአእምሮህ እንከን አልባ በልብህ ያልጎደፍህ፣ በሃሳብህ ንጹህ፣ በተፈጥሮህም የተቀደስክ ሆነህ ኑር”።*

እምነቱ ሌሎች ተጨማሪ ሕግጋትና ትዕዛዛት ሲኖሩት ከእነዚህም መካከል አልኮሆል መጠጣትንና አደንዛዥ ዕጾችን መጠቀምን መከልከል ይገኝበታል፡

ለበለጠ ማብራሪያ
ባሃኢ ማዕከል
ስልክ፡ 0116627751
ፖ.ሣ.ቁ.102 ፤ አዲስ አበባ
ኢ.ሜል፡bahais.eth@ethionet.et



# የባሃኢ እምነት

የባሃኢ እምነት ዓለም አቀፍ እምነት ሲሆን ዓላማውም ሁሉንም ዘሮችና ሕዝቦች በአንድ ሁሉን አቀፍ እቅድና እምነት ለማዋሃድ ነው። ባሃኢዎች የባሃኦላህ ተከታዮች ናቸው። ባሃኦላህም በሁሉም እምነቶች ተስፋ የተሰጠለት የእግዚአብሔር ግልጸት ነው። እንደሚታወቀው የአብዛኞቹ እምነት ትምህርቶች በመሬት ላይ ሰላምና ስምምነት የሚመሠረትበትና የሰው ልጅም በብልፅግና የሚኖርበት አንድ ዘመን እንደሚመጣ ተስፋ ይሰጣል። እኛ ባሃኢዎች ተስፋ የተሰጠለት ሰዓት እንደመጣ እናምናለን።

ባሃኦላህም የሰው ልጅ አዲስ ዓለም ለመገንባት የሚያስችሉትን ትምህርቶች አምጥቷል።

ከጽሑፎቹ በአንዱ ባሃኦላህ እንዲህ ይላል፡-

*... ጌታ ከፍተኛ ፈውስና እጅግ በጣም ታላቅ መሣሪያ አድርጎ ለመላው ዓለም መፈወሻ ያዘዘው የሕዝቦችዋን በአንድ ዓለም አቀፋዊ ዓላማ በአንድ የጋራ እምነት ሥር መሰባሰብ ነው።*

## ከባሃኡላህ ትምርቶች ጥቂቶቹ

ስለ እግዚአብሔር ሕላዌ የማይታወቅ መሆኑን ባሃኡላህ ያስተምረናል። ይህ ማለት ስለ እግዚአብሔር ምንም ዓይነት ቅርጽ በአእምሮአችን ውስጥ መቅረጽ የለብንም። በአጠቃላይ መልኩ የተፈጠረ ነገር ፈጣሪውን ሊገነዘብ አይችልም። ለምሳሌ አንድ ጠረጴዛ የሰራውን አናፂ ሊገነዘብ አይችልም።

እግዚአብሔር የሁሉም ነገሮች ፈጣሪ ነው። ባሃኡላህ እንደሚነግረን የመፈጠራችን ምክንያት ፍቅር ነው።

እንዲህ ይላል፡-

የሰው ልጅ ሆይ!

*የአንተን መፈጠር ወደድኩ፣ ስለዚህም ፈጠርኩህ። እንግዲህ ስምህን እንዳነሳና ነፍስህን በሕይወት መንፈስ እሞላት ዘንድ አንተም አፍቅረኝ።*

ስለዚህ ምንም እንኳን የእግዚአብሔር ሕላዌ ከግን ዛቤአችን ውጭ ቢሆንም ፍቅሩ ሕይወታችንንና ሕልውናችንን ሳያቋርጥ ይዳስሳል። ይህ ፍቅር ወደ እኛ የሚደርሰው በዘላለማዊው ቃልኪዳኑ አማካኝነት ነው። በዚህ ዘላለማዊ ቃልኪዳን መሠረት እግዚአብሔር ብቻችንንና ያለመመሪያ ፈፅሞ አይተወንም ።

የሰው ልጅ ከእርሱ በራቀና ትምህርቶቹን በረሳ ቁጥር እግዚአብሔር ክስተቱን ይልክና ፈቃዱንና ዓላማውን ያሳውቀናል። መክሰት የሚለው ቃል መገለፅ ማለት ነው። ከዚህ ፊት የማይታወቅን ነገር ማሳወቅ ማለት ነው። የእግዚአብሔር ግልጸቶች የእግዚአብሔርን ቃልና ፈቃድ ለሰው ልጅ የሚገልፁ ልዩ ስብዕናዎች ናቸው። ስለሆነም እነርሱን ካዳመጥን ለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ ሰጠን ማለት ነው። ከግልጸቶቹ መካከል አብርሃም፣ ሙሴ፣ እየሱስ ክርስቶስ እና ነብዩ ሙሐመድ ይገኙበታል። እኛ ላለንበት ጊዜ ከእግዚአብሔር የተላከው ግልጸት ደግሞ ባሃኡላህ ነው።

እግዚአብሔርን ልንደርስበት አንችልም፣ እነኝህ ፍፁም ሕልውናዎች ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ እኛ ይመጣሉ፣ በመካከላችን ይኖራሉ፣ መመሪያ ይሰጡናል፣ ቁሳዊና መንፈሣዊ ዕድገትን ለመቀዳጀት በሚያስፈልገን ኃይል ይሞሉናል።

የባሃኡላህ ማዕረግ የእግዚአብሔር ክብር የሚለው ነው። የባሃኡላህ ትምርቶች ከሌሎች የእግዚአብሔር ሃይማኖት ትምርቶች ጋር ፍፁም ይስማማሉ። ትምህርቶቹም የዘመናችንን የሰው ልጅ ሁኔታ የሚመለከቱ ናቸው። የሰውን ልጅ ሁኔታ ለጥቂት ጊዜ ብናስበው ሌላ የእግዚአብሔር ክስተት መምጣት ያለበት ትክክለኛው ጊዜ አሁን መሆኑን እንስማማለን። ስለምንኖርበት ቀን የሚናገር ከባሃኡላህ ጽሑፎች የሚከተለውን እናገኛለን፡-

ይህ ቀን፣ የእግዚአብሔር እጅግ በጣም የላቁ ችሮታዎች በሰዎች ላይ የፈሰሱበት፣ የእርሱ እጅግ በጣም ታላቅ ፀጋ በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ውስጥ የተናኘበት ቀን ነው። የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ልዩነቶቻቸውን በማስወገድ፣ በእርሱ እንክብካቤና ፍቅራዊ ደግነት ዛፍ ጥላ ሥር፣ በፍጹም አንድነትና ሰላም መኖር አለባቸው።

## ስለሰው ዘር አንድነት

የባሃኢ እምነት ዓላማ የሰው ዘር አንድነትን መመሥረት ነው። እኛ ሁላችንም የአንድ ዛፍ ፍሬዎችና የአንድ ቅርንጫፍ ቅጠሎች መሆናችንን የባሃኢ እምነት ትምህርቶች ይነግሩናል። ምንም እንኳን በአካልና በስሜት እርስ በእርስ የምንለያይ ቢሆንም፣ ምንም እንኳን የተለያዩ ተሰጦዎችና ችሎታዎች ቢኖሩንም ሥረ መሠረታችን አንድ ነው። ሁላችንም የሰው ዘር ቤተሰብ አባላት ነን። የሰው ዘር በአንድ ሰፊ የአትክልት ስፍራ ሊመሰል ይችላል። በዚህ አትክልት ቦታ የተለያዩ ቅርፆች፣ ቀለሞችና መዓዛ ያላቸው አበቦች፣ ጎን ለጎን ያድጋሉ። የአትክልት ሥፍራው ውበት የአበቦች፣ የተለያዩ ቀለም፣ ቅርጽና መዓዛ ውጤት ነው። ልክ እንደዚሁ በአካላዊ አቋማችን፣ በባሕሪያችን፣ ከተለያዩ ማኅበረሰቦችና ሃይማኖቶች መምጣታችን ፣ በሃሳባችንና በአስተሳሰቦቻችን መካከል ያሉት ልዩነቶች ግጭትንና ጥልን እንዲያመጡ መፍቀድ የለብንም። የሰው ዘርን ሁሉ በአትክልት ቦታ እንደሚበቅሉ ውብ አበቦች አድርገን ማየት አለብን። የዚህ አትክልት ቦታ አበቦች በመሆናችንም መደሰት አለብን።

ምንም እንኳን የሰው ዘር አንድነት የማይታበል ሐቅ ቢሆንም በምድር ላይ የሚኖሩ ሕዝቦች ከአንድነት እጅግ የራቁ ከመሆናቸው የተነሳ እነርሱን አንድ ማድረግ ቀላል ሥራ አይደለም።

አንድ ሰው የባሃኢ ማኅበረሰብን ለመቀላቀል ምርጫው ቢሆን ባሃኢዎች አንድነትን ለመገንባትና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ በምናደርገው ጥረት ተሳታፊ ይሆናል። የጦርነት ሃሳብ ሲመጣ ወዲያውኑ በሰላም ሃሳብ እንድንተካው የባሃኢ እምነት ያስተምረናል። በልባችን ውስጥ የጥላቻ ስሜት ሲቀሰቀስ ወዲያውኑ በፍቅር ስሜት መተካት አለበት። ከከንቱ ጥላቻ ነፃ ለመሆን የተቻለንን ሁሉ ማድረግ አለብን። የተሻለ ዓለምን ለመገንባት ከፍተኛ መሰናክል ከሆኑት መካከል የዘር፣ የቀለም፣ የብሔር፣ የባህል፣ የሃይማኖትና የፆታ ከንቱ ጥላቻዎች ይገኙበታል። በአንድነት ጎዳና እንዴት መጓዝ እንደምንችልና ሌሎችም ይሄንኑ መንገድ እንዲከተሉ እንዴት መርዳት እንደምንችል የባሃኢ ጽሑፎች ያስተምሩናል።

## ባሃኡላህ ማን ነው?

ባሃኡላህ በኢራን ዋና ከተማ በቴህራን እ.ኤ.አ በ1817 ተወለደ። ከልጅነቱ ጀምሮ የታላቅነት ምልክቶች ይታዩበት ነበር። ትምህርት ቤት መግባት አላስፈለገውም ምክንያቱም እግዚአብሔር መለኮታዊ ዕውቀትን አጎናጽፎት ስለነበር ነው። የወጣትነቱን ጊዜያት የተጨቆኑትን፣ ሕሙማንንና ድሆችን በመርዳት እንዲሁም ፍትህን በማራመድ አሳልፎታል።

የባሃኡላህን ታሪክ በምንዳስስበት ጊዜ ሁለት ዋና የሕይወቱን ገፅታዎች እንረዳለን። አንዱ የተቀበለው መከራ ሲሆን ሌላው ደግሞ በሰዎች ልብና አእምሮ ላይ ያሰረጸው ኃያልና መልካም ተፅዕኖ ነው። በእርግጥ ይህ በሁሉም የእግዚአብሔር ክስተቶች ሕይወት ውስጥ የሚታይ ባህሪ ነው።

የባሃኡላህ መከራ የጀመረው የእግዚአብሔርን እምነት ለማወጅ እንደተነሳ ወዲያውኑ ነበር። ሕይወቱን ሙሉ የኖረው በግዞት፣ በእስራትና በጭቆና ነበር። መጀመሪያ በቴህራን ከተማ አንድ ጨለማና ፀሐይ የማይደርስበት ጉድጓድ ውስጥ በሠንሰለት ታሰረ። ከዚያም ከአንዱ አገር ወደ ሌላው አገር አራት ጊዜ በግዞት ተንከራተተ። በመጨረሻም በኦቶማን ግዛት ውስጥ የእስር ከተማ ወደ ነበረችው እስራኤል አገር አቆር ከተማ ተጋዘ።